# “ደሞዝ የከፈለ ማዘዝ ይችላል” የሚለው አባባል በፖለቲካ ይሰራል

**ሐሙስ ታህሳስ** 21/2008 (December 31/2015) – **ግርማ ሞገስ**

==================================================================

እንደ ሰላማዊ ትግል ተማሪ ከህዳር ወር መጀመሪያ ግድም አንስቶ እስከ ታህሳስ ወር አጋማሽ 2008 ድረስ የተካሄደውን የኦሮሚያ ተማሪዎች ሰላማዊ ትግል በቅርብ ስከታተል ነበር። የሰላማዊ ትግሉ መልዕክት “የኦሮሚያን መሬት አስመልክቶ የፌደራል እና የክልል መንግስት የወጠናችሁትን እቅድ እናውቃለን ። እኛ ለእቅዳችሁ ትብብር አንሰጠውም፣ አናጸድቀውም፣ እንቃወመዋለን። እኛን እንደ ተመልካች ማየታችሁን አቁማችሁ አዳምጡን። የመሬታችን ባለቤቶች እኛ መሆናችን ተገንዝባችሁ አነጋግሩን፣ በውሳኔ መስጠቱ ሂደት አሳትፉን። የመሬታችን ተጠቃሚነት መብታችንን እወቁ።” የሚል ነበር። ካለምንም ጥርጣሬ፣ ንቀት እና እብሪት ሰልፈኞቹ የሚናገሩትን ላደመጠ እና ያነገቡዋቸውን ጽሑፎች ላነበበ ሰው የሰልፈኞቹ መልዕክት ግልጽ ነበር። ጥያቄው እጅግ በጣም ቀላል ነበር። ምንም ውስብስብነት አልነበረውም። መንግስት ግን እጅግ በሚያሳዝን አኳን ውስብስብ አደረገው።

ይህ ሰሞኑን በኦሮምያ እንደ አበባ ፈክቶ ያየነው ሰላማዊ ትግል በታሪካችን አይተነው አናውቅም። የኦሮሚያ ወጣት ህይወቱን ከፍሎ ለኢትዮጵያ ሰላማዊ ትግል ባህል እድገት ፍጹም የማይረሳ አስተዋጽኦ አድርጓል ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር ይቻላል። ይሁን እንጂ የዛሬውም ገዢ እንደ ቀድሞቹ የኢትዮጵያ ገዢዎች ሰላማዊ ሰልፈኞችን ገድሏል። ደብድቧል። አስሯል። የተጀመረው ሰላማዊ ትግል የሚቆመው ሰላማዊ ምላሽ ሲያገኝ እንጂ በግድያ እንዳልሆነ አምባገነኖች የሚገባቸው ጉዳይ አይደለም። የዚህ ጽሁፍ ግብ ሰላማዊ ትግሉን ከውድመት ጠብቀን አንድ እርምጃ ሽቅብ ከፍ ማድረግ በሚቻልበት ሁኔታዎች ላይ አንድ ሁለት የአኪያሄድ ምክሮች መለገስ ነው።

በስልጣን ላይ የሚገኝ አምባገነን ቡድን (አምባገነን መንግስት) የፖለቲካ ኃይል (አቅም) የሚፈስለት ከሰማይ ሳይሆን በምድር ላይ ከሚገኙት ስድስት (6) የፖለቲካ ኃይል ምንጮች ነው። ከእነዚህ ምንጮች የሚፈስለትን አቅም እየጠጣ መንግስት ይፋፋል። ወዛም ይሆናል። የፖለቲካ አቅሙም ይጎለብታል። ይኸን አቅም ተጠቅሞ ተቃዋሚዎቹን ይመታል። ተቀዳሚ ግቡ የሆነውን የስልጣን ዘመን ያራዝማል። ስለዚህ በመንግስት የፖለቲካ ኃይል ላይ ቀጥተኛ ጥቃት ለመፈጸም ሰላማዊ ትግል የመንግስትን የፖለቲካ ኃይል ምንጮቹን በዝርዝር ማወቅ ይኖርበታል። የመንግስትን የፖለቲካ ኃይል ምንጮች ማወቅ ለሰላማዊ ትግል ስኬት ጠቃሚ ነው።

ከስድስቱ የፖለትካ ኃይል ምንጮች ውስጥ አንዱ ምንጭ "የመንግስት የአገር ኢኮኖሚ፣ የግብር፣ የመሬት እና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነት" መሆኑ ነው። በኢትዮጵያ መንግስት የዚህ አብይ የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ባለቤት መሆኑ "ደሞዝ ከፋይ" አድርጎታል። በኢትዮጵያ ትልቁ ደሞዝ ከፋይ መንግስት ሊሆን የቻለበት ምክንያትም የዚህ ትልቅ የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ባለቤት መሆኑ ነው። ስለዚህ ለፖሊስ ከፋዩ መንግስት ነው። ለደህንነቶች ይከፍላል። ለእስር ቤቶች ሰራተኞች ደሞዝ ከፋይ ነው። ለመንግስት ሚዲያ ሰራተኞች ደሞዝ ከፋይም እሱ ነው። ለመለዮ ለባሹ ደሞዝ ከፋይ እሱ ነው። ለካድሬዎችም ይከፍላል። ሁልጊዜም ባይሆን አስተዳደሩን ለማጠናከር እና የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም ደሞዝ የከፈላቸውን ሁሉ ያዛል። ሁሉም ይታዘዛሉ። ሁልጊዜ ባይሆንም።

ማን የዚህ ቁልፍ የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ባለቤት አደረገው ? ህዝብ ዴሞክራሲያዊ በሆነ ስርዓት ፈቅዶ የለገሰው እንዳልሆነ ይታወቃል። ከዚህ የፖለቲካ ኃይል ምንጭ የሚፈስለት አቅም እንዲዳከም

ከተደረገ መንግስት ደሞዝ የመክፈል አቅሙ እንደሚዳከም ግልጽ ነው። እንደቀድሞው ደሞዝ መክፈል አይችልም። ደሞዝ ያልተከፈላቸው አብዛኛው ካድሬ፣ ፖሊስ፣ ደህንነት፣ የእስር ቤት አስተዳዳሪ፣ ቢሮክራሲው (የተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤት ሰራተኛ) እንደቀድሞ መታዘዝ አይፈልጉም። "ደሞዝ ያልከፈለ" ማዘዝ አይችልም ማለት ነው። ስለዚህ መንግስት ደሞዝ ሳይከፍ እንደቀድሞው ማስተዳደር እንደማይችል ግልጽ ነው።

ደሞዝ እስካልከፈለ ድረስ የሚታዘዝለት ስለማይኖር መንግስት እንደቀድሞው ተቃዋሚውንም መምታት አይችልም። በዚህ አይነት ቀደም ሲል በመንግስት እና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል የነበረው የበላይነት እና የበታችነት ግንኙነት የፖለቲካ አቅም ሚዛን ይቀየራል። በመጨረሻም የመንግስት ደሞዝ መክፈል አቅም መዳከም ቀጣይነት እንዲኖረው ከተደረገ በመንግስት እና በተቃዋሚዎች መካከል የነበረው የፖለቲካ ኃይል ሚዛን ግንኙነት ከበላይ እና ከበታች ግንኙነት ወደ አቻነት እንደሚሸጋሸግ ግልጽ ነው።

ከአገር ውስጥ እና ከውጭ ወደ መንግስት የሚፈሰው የገንዘብ መጠን ከቀነሰ ደሞዝ የመክፈል አቅሙ እንደሚቀንስ ግልጽ ነው። ይኽ ጉዳይ እንግዲህ ሰላማዊ ትግሉን ቀስ በቀስ በኢኮኖሚ ግንባር ትብብር ማሸጋገርን የግድ ይላል።

በመጨረሻ በኢትዮጵያ በመደረግ ላይ የሚገኘውን ሰላማዊ ትግል በሚመለከት ሁላችንንም ሊያሳስቡን እና ጥንቃቄ ልናደርግባቸው የሚገቡ ሶስት ማስጠንቀቂያ መሰል ነገሮች ልናገር እና ልሰናበታችሁ። እነሱም አንደኛው ግብታዊነትንት (Spontaneity)፣ ሁለተኛው ብክለት (Contamination) የሚለው ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ ህብረት ወይንም ለነፃነት የሚደረግ ሰላማዊ ትግል ትግግዝ (ሽርክና) የሚለው ነው።

**ግብታዊነት፥**

(1) ግብታዊ ሰላማዊ ትግል አምባገነኖች ሊወስዱዋቸው የሚችሉትን አረመኔያዊ እርምጃዎች በቅድሚያ የመገመት እና የመዘጋጀት ጊዜ ስለሌለው ግብታዊነትን ልናስወግድ ይገባል።

(2) ግብታዊ ሰላማዊ ትግል ሊገጥሙት የሚችሉትን ወሳኝነት ያላቸው እንቅፋቶች በቅድሚያ አንስቶ ተገቢ ፕላን ስለማ ያሰላ ውጤቱ ውድመት ሊሆን ስለሚችል ግብታዊነት ሊወገድ ይገባል።

(3) ግብታዊ ሰላማዊ ትግል በስልጣን ላይ የሚገኘውን አምባገነን መንግስት ማውረድ ቢችልም ቀደም ብሎ የተሰላ ህዝ ብን የመንግስት ስልጣን ባለቤት የሚያደርግ እና ምናልባትም በሽግግር ወቅት ለከሰት የሚችልን በመፈንቅለመንግስት ወይንም በራሱ ከስልጣን በወረደው ቡድን የሚፈጸመን ቅልበሳ የሚከላከል ፕላን ስላማይኖረው አገሪቱን ወደ ነፃ ምርጫ እና ወደ ዲሞክራሲ ማሸጋገር ስለሚሳነው ህዝብን የ ድል ባለቤት ማድረግ አይችልም። አዲስአምባገነን የድል ፍሬ ሰብሳቢ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ግ ብታዊነትን እናስወግድ።

ስለዚህ አንድን ሰላማዊ ትግል ግብታዊ ነው ከሚያሰኙት መስፈርቶች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ግብታዊ ሰላማዊ ትግሎች ሊነሱ ከሚችሉባቸው ምክንያቶች ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፥

(1) በተለያዩ የመንግስት ስልጣን እርከን የሚገኙ ሙስና የተጠናወታቸው አምባገነኖች በቃኝ የማ ይለውን የግል ፍላጎታቸውን ለማሙዋላት በህዝብ ላይ የሚፈጽሟቸው አይን ያወጡ አስገዳጅ ዘረፋ ዎች እና ጨቋኝ ተግባራት ህዝብሊሸከም ከሚችለው መጠን ሲያልፉ፣

(2) በተለያዩ የመንግስት ስልጣን እርከን ላይ የሚገኙ አምባገነን አለቆቻቸውን በማስደሰት ተሿሚ እና ተሸላሚ ከመሆን በስተቀር ሌላ የማይታያቸው እውር ሹመኞች በህዝብ እና በታዋቂ ግለሰቦች ላይ የሚወስዱዋቸው አረመኔእርምጃዎች ህዝቡን ሲያስቆጡ፣
እንደሚታወቀው ለተጀመረው ግብታዊ ሰላማዊ ህዝባዊ አመጽ መንግስት ፍትሃዊ ምላሽ ካልሰጠ ሰላማዊውን አመጽ አባብሶ ገዢውንም ሆነ ተቃዋሚውን (ሁለቱንም) ሊያሰምጥ የሚችል ሁኔታ ለ ፈጠር ይችላል።

**ብክለት፥**
ሰላማዊ ትግሉን ከብክለት መጠበቅ ሌላው የሰላማዊ ትግል የደህንነት ስራ ነው። ጀብዱኛ ግለሰቦች ወይንም ሌሎች ሰላማዊ ትግሉን ተቀላቅለው የሶሪያ አይነት ሁኔታ በኢትዮጵያችን እንዳይደገም ማድረግ አለበን። ሰላማዊ ትግሉ በፕላን የሚመራ እና በሰላማዊ ትግል ድስፕሊን እየታነጸ እንዲያድግ ማድረግ አለብን። ሰላማዊ ሰልፈኞች መካከል ሆኖ ፖሊስ ላይ ድንጊያ መወርወር ወይንም ጥይት መተኮስ ሰላማዊ ትግል አለመሆኑ በግልጽ መታወቅ አለበት።

**ህብረት/ሽርክና፥**
ይህ ማለት የድርጅት ውህደት ሳይሆን በተጨባጭ መንግስት በሰላማዊ ትግሉ ላይ የሚፈጽመው እና የአገሪቱ የሰላማዊ ትግል ሰራዊት በአንድ ጥላ ስር መሰባሰብን አስተውሎ አዎንታዊ ምላሽ የሚሰጥ በጋራ ግብ ዙሪያ መሰባሰብ ማለት ነው። የአይዲዮሎጂ እና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ከተፈጠረ በኋላ የዴሞክራሲ ኃይሎች በመነጋገር ወይንም በድርድር ወይንም ህዝቡ በምርጫ ፖሊሲ ልዩነቶች ላይ በሚሰጠው ድምጽ ሊወሰኑ የሚችሉ ጉዳዮችን አለጊዜያቸው አንስቶ አለመራኮት ማለት ነው። ውህደትም ቢሆን ለረጅም ጊዜ በትናንሽ ጉዳዮች ላይ ተጋግዞ በመስራት የሚፈጠር ትውውቅን ቅድሚያ ይላል። በጋራ መስራት በጋራ መስራት የሚቻሉ ነገሮችን ለይቶ አውጥቶ በእነሱ ላይ ተጋግዞ አብሮ የመስራት ባህልን መገንባት መጀመርን የግድ ይላል። በተፈጥሮው የትጥቅ ትግል በመግደል አሸናፊ ፓርቲ መፍጠርን የግድ ስለሚል የተቃዋሚ ፓርቲዎችን አብሮ መስራት አዳጋች ያደርጋል። ሰላማዊ ትግል ግን በተፈጥሮው ያን አይነት ችግር የለውም። በዚህ ረገድ በአሁኑ ሰዓት ጉልህ የሆነ የህዝብ ድጋፍ ያላቸው ሰማያዊ ፓርቲ እና መድረክ አብረው መስራት የማይችሉበት ምክንያት ፍጹም አይታየኝም። እነዚህ ሁለት ፓርቲዎች አብረው በመስራት የህዝባቸውን ጥም ማርካት አለባቸው። አብረው በመስራት ብስለታቸውን ለህዝባቸው ማሳየት አለባቸው። ይህን በማድረግ የህዝባቸውን ክብር እና ምስጋና ማግኘት ይገባቸዋል። በአጭሩ በርቀት ማስተዋል የሚችሉ መሪዎች መሆናቸውን ሊያሳዩን ይገባል።

ከሰላምታ ጋር
ግርማ ሞገስ

Ethiomedia.com – December 31, 2015